# የአንድነት ሥራ አስፈፃሚ አቶ ታምራት ታረቀኝን ከፓርቲው አገደ

**- የፓርቲውን ምስጢር በማውጣት ተጠርጥረዋል**

እጅግ ተደጋጋሚ በሆነ ስብሰባ የተወጠረውና የፓርቲውን ምስጢር የሚያወጡ ግለሰቦችን ለመለየት ኮሚቴ ያቋቋመው የአንድነት ፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣አስራ አንድ አባላት አስቸኳይ ስብሰባ በማድረግ የፓርቲው የሥራ አስፈፃሚ አባልና የወጣቶች ዘርፍ ኃላፊ የነበሩትን አቶ ታምራት ታረቀኝን ማገዱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

እንደ ኢትዮ-ቻናል የመረጃ ምንጭ፣ አቶ ታምራት የታገዱት ከስራ አስፈፃሚ አባልነታቸውና ከጽ/ቤት ኃላፊነታቸው ሲሆን ደመወዛቸውም የማይከፈል መሆኑ ታውቋል፡፡

የሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ አባላት ይህንን ውሳኔ ለመወሰን የቻሉት እንደ መረጃ ምንጮቻችን ዘገባ ከሆነ የፓርቲውን ሚስጢር የሚወጣበትን መንገድ እንዲያጠና የተመረጠው ኮሚቴ አቶ ታምራት የፓርቲውን ምስጢር ያወጣሉ የሚል ኮሚቴው ባቀረበው ሪፖርት መነሻ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የግንቦት 7 ንቅናቄ አባላት ሲሆኑ ይችላሉ የተባሉና የአንድነት ፓርቲን ሊበትኑ ያቅዳሉ ተብለው የተጠረጠሩት አምሣ ዳኜ፣ ታምራት ታረቀኝ፣ አለባቸው አያሌው፣ የሺዋስ አሰፋ፣ አምበሉ አለማየሁ እና ይልቃል ጌትነት የተባሉት የፓርቲው አባላት ላይ የማጣራት ስራ ሲሰራ የነበረው ቀደም ሲል የተቋቋመው አጣሪ ኮሚቴ አሁንም በግለሰቦቹ ላይ የተጠናከረ የማጣራት ስራውን እንዲቀጥል ስራ አስፈፃሚው ውሳኔ አስተላልፏል፡፡